መግለጫ ዜና

Edward B. Murray፣ ከንቲባ
Christopher Williams፣ ጊዜአዊ ዋና ሃላፊ

በአስቸኳይ የሚሰራጭ ጥር 9, 2014

ተጠሪ፥ Joelle Hammerstad (206) 684-8020
ኢሜይል joelle.hammerstad@seattle.gov

የሲያትል መናፈሻ ቦታዎች ጽ/ቤት፣ የዜጎች ኮሚቴ ስለታቀደው የመናፈሻ ቦታ ሥራ ማካሄጃ የድምጽ ውሳኔ ከማህበረተሰቡ ጋር ስብሰባ ያደርጋል

የሲያትል መናፈሻ ቦታዎች እና መዝናኛ ጽ/ቤት፣ የ Parks Legacy Citizens' Advisory Committee ለ 2014 ዓመት ለታቀደው የመናፈሻ ቦታና መዝናኛ ሥራ ማካሄጃ የድምጽ ውሳኔ ለመዘጋጀት ስላከናወነው ሥራ ገንቢ ሃሳብ ለማግኘት ሦስት የማህበረተሰብ ስብሰባዎችን ያስተናግዳል።

ስብሰባዎቹ የሚካሄዱት፥

- ሐሙስ፣ ጥር 23፣ ኢንተርናሽናል ዲስትሪክት/ቻይናታወን ኮሚኒቲ ሴንተር፣ 719 8th Ave. S, ከሰዓት 6 ሰዓት
- ቅዳሜ፣ ጥር 25፣ ሃይፖይንት ኮሚኒቲ ሴንተር፣ 6920 34th Ave. SW, ከሰዓት 1 ሰዓት (ነጻ የመዋለ ሕጻናት አገልግሎት (ቻይልድኬር) ይቀርባል)
- ሐሙስ፣ ጥር 30፣ ቢተር ሌክ ኮሚኒቲ ሴንተር፣ 13035 Linden Ave. N, ከሰዓት 7 ሰዓት

ስብሰባዎቹ ኮሚቴው እንዴት ለታቀዱ የመዋለ ንዋይ (ኢንቨስትመንት) ሃሳብ ዝርዝሮች ቅድሚያ እንደሰጠ የሚገልጽ አጭር መግለጫን ይመለከታሉ። ከዚያም ቀጥሎ የማህበረተሰቡ ሃሳብ እንዲሰጥባቸው በሚያስፈልጋቸው በሦስት ልዩ ነጥቦች ላይ በባለሙያዎች የሚስተናገዱ የሥራ ጥናቶች ይካሄዳሉ።

1. <u>ቅድሚያ የሚሰጣቸው ነገሮች።</u> ኮሚቴው ስለሚከተሉት ትክክለኛውን ሚዛን አውቋል፥ 1) የከተማው ማዘጋጃ ቤት አሁን በንብረትነት የያዛቸውን የመናፈሻ ቦታና መዝናኛ ንብረቶች መንከባከብ፤ 2) ለማህበረተሰቡ ፕሮግራሞች፣ ትምህርቶችና አገልግሎቶች ሥራ ማካሄጃ ገንዘብ ማቅረብ፤ እና 3) "በመሬት የተከበቡ" የመናፈሻ ቦታ ንብረቶችን አዲስ መናፈሻ ቦታዎች እንዲሆኑ በመገንባትና አዲስ የመናፈሻ ቦታ መሬት ባለንብረት በመሆን ለወደፊት መዘጋጀት?
2. <u>መጠን።</u> የስብሰባው ተካፋዮች እንዴት የተለያዩ ሥራ ማካሄጃ ደረጃዎች የቤት ባለንብረት ግብርን እንደሚነኩ ትምህርት ይቀስማሉ፣ እናም ከዚያ የትኛው የሥራ ማካሄጃ መጠን ተገቢ ሊሆን እንደሚችል ገንቢ ሃሳባቸውን ያቀርባሉ።
3. <u>የሥራ ማካሄጃው መንገድ።</u> የስብሰባው አስተናጋጆቹ በአጭር-ጊዜ፣ በረጅም-ጊዜ፣ እና በቋሚ ግብር ክፍያዎች መካከል ስላሉት ልዩነቶችና፣ ልዩነቶቹ የሜትሮፖሊታን ፓርክስ ዲስትሪክትን (MPD) ከማዘጋጀት ጋር እንዴት እንደሚወዳደሩ ያብራራሉ። ከዚያም የስብሰባው ተካፋዮች ለሲያትል በጣም ተስማሚ ለሆነው መንገድ ገንቢ ሃሳባቸውን እንዲሰጡ ይጠየቃሉ፣ እንዲሁም ስለ እያንዳንዱ አማራጭ ሃሳባቸውን ወይም አሳሳቢ ጉዳያቸውን እንዲገልጹ እድል ይሰጣቸዋል።

የሲያትል መናፈሻ ቦታዎች እና መዝናኛ ጽ/ቤት ከአንድ ዓመት በፊት በ Park Legacy Plan ጉዳይ ላይ ሥራ ጀምሯል፣ እሱም ለሥራ ማካሄጃ የድምጽ ውሳኔ መሠረት ይሆናል። ሂደቱ የተጀመረው በተከታታይ የማህበረተሰብና የመናፈሻ ቦታ-ተጠቃሚ ጥናቶች ሲሆን፣ ከመላው ከተማ ሃሳቦችን ለማሰባሰብ በስድስት የሕዝብ ስብሰባዎች ተጠናቋል። ሂደቱ ያተኮረው እንዴት የሲያትል መናፈሻ

ቦታዎች እና መዝናኛ ጽ/ቤት እንቅስቃሴ በተሞላበት ከተማ እየጨመረ የሚመጣ ፍላጎትን ማሟላት እንደሚቻል የብዙ ሰዎች ድምጽን ለውይይት በማቅረብ ላይ ነበር።

የሲያትል መናፈሻ ቦታዎች ጽ/ቤት በ ሰኔ 2013 ውስጥ የ Parks Legacy Plan ሁለተኛውን ረቂቅ ጽሁፍ ካሳተመ በኋላ፣ ከንቲባውና የከተማው ምክርቤት የመናፈሻ ቦታ ሥራ ማካሄጃ ድምጽ ውሳኔ (ባሎት ሜዝፐር) ምን ያህል የገንዘብ መጠን መክፈል እንዳለበት እና በምን ዓይነት የሥራ ማካሄጃ መንገድ – የግብር ክፍያ (ለቪ) ወይም ሜትሮፖሊታን ፓርክስ ዲስትሪክት መሆን እንዳለበት እንዲያማክራቸው አንድ የፈቃደኞች Parks Legacy Citizens' Advisory Committee ስብሰባ አድርገዋል።

በታህሳስ ወር ውስጥ፣ ኮሚቴው የመጀመሪያውን ዘገባ እና የሥራ ማካሄጃ ያስፈልጋቸዋል ብሎ የሚያምንባቸውን ቅድሚያ የሚሰጣቸውን የፕሮግራሞችና አገልግሎቶች ዝርዝር የመጀመሪያ ረቂቅ አውጥቷል። በእያንዳንዶቹ ስብሰባዎቹ ላይ፣ ኮሚቴው ከሕዝብ ሃሳብ የተቀበለ ሲሆን፣ በጎዳር ወር ውስጥም የሕዝብ ስብሰባ አድርጓል።

በጥር ወር የማህበረተሰብ ስብሰባዎች ላይ፣ ሕዝቡ ኮሚቴው ሃሳብ ስላቀረበባቸው ጉዳዮች በይበልጥ ያውቃል፣ ሊኖሩ ስለሚችሉ የሥራ ማካሄጃ አማራጮች ትምህርት ይቀስማል፣ እንዲሁም የኮሚቴ አባላትን አግኝቶ ውይይት ያደርጋል።

ከጥር ወር የማህበረተሰብ ስብሰባዎች በኋላ፣ ከሕዝብ በቀረው ሃሳብ መሠረት የመጀመሪያዎቹን ሃሳቦች ለመገምገምና ምናልባትም ለመከለስ በየካቲት ወር ውስጥ ኮሚቴው እንደገና ይሰበሰባል፤ እንዲሁም ስለሥራ ማካሄጃው መጠንና ዓይነት ውይይት አድርጎ ሃሳብ ያቀርባል። ኮሚቴው ማጠቃለያ ሃሳቡን በመጋቢት 12 ላይ ለከንቲባውና ለከተማው ምክር ቤት ይልካል።

የኮሚቴው አባላት፥ Barbara Wright, ሊቀመንበር፤ Charlie Zaragoza, ሊቀመንበር፤; Thatcher Bailey; Steve Daschle; Juli Farris; Bill Farmer; Thomas Goldstein; Jessie Israel; Diana Kincaid; Michael Maddux; Brice Maryman; Yalonda Gill Masundire; Mustapha Math; Erika Melroy; እና David Namura.

በይበልጥ ለማወቅ፣ የ Legacy Committee's Interim Report (የኮሚቴ ጊዜያዊ ዘገባ) ያንብቡ። በ www.seattle.gov/parks/legacy/committee, ወይም የጽሑፍ ቅጂ ከማህበረተሰብ ማዕከላትና መዋኛ ቦታዎች ሊያገኙ ይችላሉ። ጊዜያዊው ዘገባ የኮሚቴውን ሂደት፣ መሠረታዊ ሃሳብ፣ እና ስለቀረቡ ጊዜያዊ ሃሳቦች በዝርዝር ይገልጻል።

ስለ እያንዳንዱ ዕቅድ መዋለ ንዋይ (ኢንቨስትመንት) እና ሊኖሩ ስለሚችሉ የሥራ ማካሄጃ መንገዶች ዝርዝር መረጃ በ Parks Legacy Citizens' Advisory Committee ዌብሳይት ላይ ይገኛል፣ እንዲሁም በስብሰባዎቹ ላይ ይገኛል።

ሃሳባቸውን ማቅረብ ለሚፈልጉ፣ ግን ለስብሰባዎች መምጣት የማይችሉ ሰዎች አስተያየት ሃሳባቸውን በጽሑፍ መስጠት ይችላሉ፣ በጽሑፍ የሚቀርበው ሃሳብ በቃል እንደሚሰጠው አስተያየት ሃሳብ እኩል ክብደት ይሰጠዋል። እባክዎን አስተያየት ሃሳብዎን በኢሜይል ለ parkslegacy@seattle.gov ይላኩ።

ለቃል ትርጉም አገልግሎቶች ወይም በስብሰባው ላይ ለልዩ መስተንግዶ፣ እባክዎን ለ parkslegacy@seattle.gov ኢሜይል ይላኩ ወይም ለ Susanne Rockwell በ (206-733-9702) ይደውሉ።

# # #